# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 130 ህዳር 2 ቀን 2003 ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

**የወቅቱ የግንቦት 7 የትግል ጥሪ**

**“የጋራ ውርደት እንዲያከትም እብሪተኞችን በጋራ እምቢ እንበል፤ ዘረኛውና አዋራጁን የወያኔ ስርዓት ለማስወገድ በጋራ እንነሳ!!!:”**

**ጥርሱን አግጦ ለወጣ የአምባገነኖች የምርጫ ለበጣ ምላሹ “እምቢ ለመብቴ!!!” ብቻ ነው**

## በኖርዌይ ኦስሎ ሂዩማን ራይትስ ዋች ስለ ኢትዮጵያ ባወጣው ሪፖርት ላይ ውይይት ተካሄደ

ባለፈው ሰኞ ኖቨምበር ስምንት ቀን 2010 ዓም በኖርዌይ ኦስሎ ከተማ የኖርዌይ ዓለም አቀፍ ህግና ፖሊሲ ኢንስቲትዩት ያዘጋጀውና Development without Freedom How Aid Underwrites Repression in Ethiopia በሚል ርእስ ሂዩማን ራይትስ ዋች በቅርቡ ባወጣው ሪፖርት ላይ ያተኮረ ወርክሾፕ ተካሄደ። በስብሰባው በርካታ ኢትዮጵያዊያን፤ ተጋባዥ እንግዶች፤ የኖርዌይ መንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት እንዲሁም የተለያዩ ርዳታ ሰጪ ድርጂት ወኪሎች የተገኙ መሆኑን የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ከስፍራው ባስተላለፈው ዘገባ አሳውቋል።

በእለቱ ሂዩማን ራይትስ ዋች ያወጣውን ሪፖርት ለውይይት ያቀረቡት በድርጅቱ ከፍተኛ ተመራማሪና የአፍሪቃ ቀንድ ቡድን መሪ ሌዝሊ ሌፍኮ ሲሆኑ፤ በውይይቱ የኖርዌይ መንግስት ስቴት ሴክሬታሪ ኢንግሪድ ፊስካ፣ በቅርቡ የሂዩማን ራይስት ዋች የዓመቱ ምርጥ ተሸላሚ የሆነው ኢትዮጵያዊው ዮሴፍ ሙሉጌታ፤ የኖርዌይ ዓለም አቀፍ ህግና ፖሊሲ ኢንስቲትዩት ኤክስፐርት ፕሮፌሰር ሼትልና ሌሎችም በርካታ ተሳታፊዎች ተገኝተው ነበር።

ሌዝሊ ሌፍኮ ሪፖርቱን አስመልክቶ ባቀረቡት አጭር ማብራሪያ በኢትዮጵያ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታና ኢትዮጵያውያን ያሉበትን እጅግ አስከፊ ገጽታ፤ የወያኔው አገዛዝ በምን አይነት መልክና ሁኔታ ለልማት ርዳታ እየተባለ ከውጭ ሃገራት መንግስታት የሚጎርፍለትን ገንዘብ ለፖለቲካ ፍጆታ እንደሚያውል በተጨባጭ ማስረጃዎች በማስደገፍ ተሳታፊዎችን ባረካ መልኩ ማብራሪያ ሰጥተዋል። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## ዘረኛው እና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ሲገለበጥ በትግራይ ተወላጆች ላይ ሊደርስ የሚችለው አደጋ ስጋት እየፈጠረ ነው

ጄኖሳይድ ዋች የተባለው የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅት ፕሬዚደንት የሆኑት ዶ/ር ግሬጎሪ ስታንተን፤ በዋሽንግተን ዲሲ የሰማእታት መታሰቢያ ዝግጅት ላይ ተገኝተው ባደረጉት ንግግር፣ የወያኔ አገዛዝ ሲወድቅ ለወንጀሉ የሚከፍለው የትግራይ ህዝብ እንዳይሆን እሰጋለሁ ብለዋል።

“ከጥንት ስልጣኔዎች ውስጥ አንዷ የሆነችው ኢትዮጵያ፤ በአሁኑ ሰዓት በአረመኔያዊ አገዛዝ እየተመራች ነው” በሚል ንግግራቸውን የጀመሩት ዶ/ር ግሬጎሪ፤ አሁን ያለው ሁኔታ የትግራውያን የበላይነት የተረጋገጠበት በመሆኑ፤ ለዚህ የሚከፍሉት እና የሚጠሉት የትግራይ ተወላጆች ናቸው ሲሉ ስጋታቸውን ገልጸዋል።

ዘረኛውና አምባገነናዊው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ፤ በተወሰኑ ምርጥ ትግራውያን ድጋፍ በኢትዮጵያውያን ላይ የሚፈጽመው ግፍ እና ዘረፋ እየፈጠረ ያለው ቁጣ ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ እንደሄደ አሰተያየት ሰጪዎች ይናገራሉ። በርካታ ኢትዮጵያውያንም፣ የትግራይ ምሁራን ለነፃነት የሚደረገውን ትግል በጉልህ ሁኔታ ከወዲሁ ካልተቀላቀሉ፤ አገዛዙ ከስልጣን ሲወገድ ስሜታዊ የበቀል እርምጃዎች ሊቀሰቀሱ እንደሚችሉ ያላቸውን ስጋት ሲገልጹ ቆይተዋል።

ዶ/ር ግሬጎሪ፥ ከዚህ ቀደም በሩዋንዳ እና በቡሩንዲ ኖረው እንደሚያውቁ ገልጸው፤ ከአንድ ዘር ብቻ የተውጣጡ ልሂቃን አንድን አገር ሲቆጣጠሩ የሚደርሰውን አደጋ ለመመልከት እንደቻሉ በማስረዳት፤ አሁን የሚሰጉት ለማንም ሳይሆን ለትግራይ ብቻ እንደሆነ አስረድተዋል።

ከጥቂት ሳምንታት በፊት የቀድሞ የመለስ ዜናዊ አማካሪ የሆኑት የትግራይ ምሁር ፕሮፌሰር ተኮላ ሃጎስ፤ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በኢትዮጵያ እና በህዝቧ ላይ የሚፈጽማቸውን ግፎች ያለ ትግራውያን እርዳታ ሊያደርገው ባልቻለ ነበር ሲሉ ብዙዎችን ያስገረመ ጽሁፍ አውጥተዋል። ፕሮፌሰሩ፥ የትግራይ ተወላጆች የተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ የሚያደርገውን ትግል በመቀላቀል ከወዲሁ ጎራ እንዲመርጡ ጥሪ አቅርበው እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም።

## በድህረ-ምርጫ 97 የወደቁትን ሰማእታት ለማሰብ የተሰናዱ ዝግጅቶች በአለም ዙሪያ ተካሄዱ

በጥቅምት 1998 አመተ ምህረት፤ በዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ ቀጥተኛ ትእዛዝ በአጋዚ ጦር የተጨፈጨፉትን ሰማእታት ለማሰብ ከተሰናዱት እና አንድ ወር ሙሉ ከሚካሄዱት ዝግጅቶች ውስጥ የመጀመሪያዎቹ እሁድ ኖቬምበር 7 ቀን በተለያዩ የአለማችን ክፍሎች ተካሄደዋል።

በሰሜን አሜሪካ፣ በአውሮፓ፣ በአፍሪካ፣ በአውስትራሊያ እና በመካከለኛው ምስራቅ ከተሞች የመታሰቢያ ዝግጅቶች የተካሄዱ ሲሆን፤ በአሜሪካ ዋና ከተማ ዋሽንግተን ዲሲ የተዘጋጀው ስብሰባ በተሳካ ሁኔታ ተከናውኗል። በመቶዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች በተሳተፉበት ዝግጅት ላይ ተገኝተው ንግግር ካደረጉት መሃል ዳኛ ፍሬህይወት ሳሙኤል፤ ዶ/ር አክሎግ ቢራራ፤ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፤ ዶ/ር ግሬጎሪ እስታንተን እና የጋራ ንቅናቄ ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ የተባለው ድርጅት መስራች እና ዋና ዳይሬክተር አቶ አባንግ ሜቶ ይገኙበታል።

በድህረ ምርጫ 97 የተካሄዱትን ግድያ እንዲያጣራ የተቋቋመው ኮሚቴ ሊቀመንበር የነበሩትና በአሁኑ ሰዓት በስደት ላይ የሚገኙት ዳኛ ፍሬህይወት ሳሙኤል፣ “የህግ የበላይነት መጥፋት፤ አንድም ሰው ለፍርድ ያለመቅረቡ… ይረብሻል። የመኖር ዋስትና ያሳጣል” ብለዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢዎች ቡድን ባለፈው አመት የምርጫ ተውኔት ላይ ባወጣው ሪፖርት የወያኔን አገዛዝ ክፉኛ አወገዘ

የህብረቱ የምርጫ ታዛቢዎች ቡድን የግንቦት 15፣ 2002ቱን የምርጫ ተውኔት ሪፖርት ከአምስት ወራት በኋላ በብራሰልስ ከተማ ይፋ ማድረጉን የዝግጅት ክፍላችን ባልደረባ ከስፍራው በላከው ዘገባ አሳውቋል።

ቡድኑ በዘረኛው እና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ላይ ጠንካራ ሂሶችን የሚሰነዝረውን ሪፖርት በአዲስ አበባ ለማቅረብ ፈልጎ የመግቢያ ፈቃድ እንደተከለከለ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፤ ይህም በአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢነት የረዥም አመታት ልምድ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የተከሰተው በኢትዮጵያ መሆኑን ሪፖርተራችን የቡድኑን መሪ ጠቅሶ ዘግቧል።

የግንቦት 15ቱን ምርጫ ተብዬ በማስመልከት የወጣው ሪፖርት፤ ቡድኑ ከዚህ ቀደም ያለውን የሚያስረግጥ ሲሆን፤ ምርጫው አለማቀፍ መስፈርቶችን እንደማያሟላ፤ በተካሄደበት ወቅትም የፖለቲካ ምህዳሩ ጠባብና የውድድር ሜዳው ለገዢው ቡድን ያደላ እንደነበር መስክሯል። በተጨማሪም፥ እንደከዚህ ቀደሙ ሁሉ ገዢው ቡድን የመንግስት ንብረት ለምርጫ ቅስቀሳ ሲጠቀም እንደነበር፤ የግል መገናኛ ብዙሃን እና የሲቪኩ ማህበረሰብ ከደረሰባቸው አፈና የተነሳ መንቀሳቀስ አለመቻላቸውን ገልጿል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በርካታ የፌደራል ፖሊስ አባላት በዘረኛነት ምክንያት ስራቸውን እየለቀቁ እንደሆነ ተዘገበ

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን - ኢሳት - በስራ ቦታ ዘረኛነት ምክንያት ስራቸውን እየለቀቁ የሚጠፉ የፌዴራል ፖሊስ አባላት ቁጥር ከመቼውም ጊዜ በላይ ጨምሯል ሲል የአዲስ አበባ ምንጮቹን ጠቅሶ ዘግቧል።

በተለያዩ ወረዳዎች የፌደራል ፖሊስ አባላትን ለመቅጠር ማስታወቂያዎች የተለጠፉ ሲሆን፣ እስከዛሬ ድረስ ብዛት ያላቸው አመልካቾች አለመምጣታቸውንም ዘገባው ገልጿል።

የኢሳት ዘጋቢ አንዳንዶቹን ፖሊሶች ጠይቆ ለመረዳት እንደቻለውም፤ በመስሪያ ቤቱ ውስጥ የሰፈነው በዘር ላይ የተመሰረተ አሰራር ስራቸውን ለመልቀቅ አስገድዷቸዋል። እድገት፣ ሹመት፣ እና የስራ ምድብ በተወሰኑ ብሄር አባላት ችሮታ እንደሚሰጥ የሚናገሩት (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በምርጫ ታዛቢው ሪፖርት መደሰታችን በኅብረቱና መንግሥታቱ ፓሊሲ ላይ ያለንን ቅሬታ አይለውጥም!!!

የአውሮፓ ኅብረት የኢትዮጵያ ምርጫ 2002 ታዛቢዎች የተልዕኮው ማጠቃለያ ሪፖርት አቅርቧል። ቡድኑ የ2002ቱ የህዝብ ተወካዮችና የክልል ምክር ቤቶች ምርጫ “ለምርጫ የተቀመጡ ዓለም ዓቀፋዊ ግዴታዎችን ያላሟላ ነበር” ሲል ደምድሟል።

የታዛቢ ቡድኑ በሪፓርቱ ምርጫው “አስፈላጊ በሆነው የሂደቱ ክፍል ውስጥ ግልጽነትና ለሁሉም ተቃዋሚዎች የተመቻቸ የመጫወቻ ሜዳ ማዘጋጀት ያለመቻል ጉድለት ነበረው። የበለጠ ተገቢ እና ወካይ የምርጫ ሂደት ለማረጋገጥ የሚያስችል የምርጫ ሂደትን ለማረጋገጥ የሚያስችል በቂ የሆነ ጥረት አልተደረገም” ሲል ተችቷል።

ከዚህም በተጨማሪ

- መራጩ ህዝብ የገጠመውን የመረጃ አፈና፤
- የምርጫ ቦርድ የተፎካካሪ ፓርቲዎችን አመኔታ ማጣት፤
- ገዢው ፓርቲ የመንግሥትን ንብረት ለምርጫ ቅስቀሳ መጠቀሙ፤
- በመንግሥትና በፓርቲ መካከል ድንበር አለመከለሉ፤ እና

በድምጽ ቆጠራና በድምጽ ማስታወቅ ወቅት በርካታ ጉድለቶች መታየታቸው በሪፓርቱ ላይ ተተንትኗል።

በማጠቃለያም ቡድኑ ለወደፊቱ ቢደረጉ ይበጃሉ ያላቸውን የማሻሻያ ነጥቦችን አቅርቧል። ካቀረባቸው የማሻሻያ አስተያየቶች ውስጥ፡-

1. የተቃዋሚዎችን ተሳትፎና ብቃት ለማሳደግ እና የፓለቲካ ምህዳሩን ለማስፋት አንድ በስደት ላይ የሚገኙ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪ እንዲመለሱ እና የታሰሩት እንዲፈቱ፤
2. በገዢ ፓርቲና በመንግሥት መካከል ግልጽ የሆነ ልዩነት እንዲኖር፤
3. የመራጮችና የተመራጮች ምዝገባ ግልጽነት እንዲኖረው እና ምዝገባው በኮምፒዩተር የታገዘ እንዲሆን፤ እና
4. ብሄራዊ የምርጫ ቦርድ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አመኔታ ያለው ተቋም እንዲሆን የሚሉ ይገኙበታል።

የአውሮፓ ኅብረት የምርጫ ታዛቢዎች ቡድን ተልዕኮዉን በብቃት ስላከናወነ ሊመሰገን ይገባል። ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ለልዑካኑ ቡድን መሪ ሚስተር ቲጅስ በርማን እና ባልደረቦቻቸው ያለውን አክብሮት ይገልፃል።

ይሁን እንጂ የአውሮፓ ኅብረትና የአውሮፓ መንግሥታት በዚህ ሪፓርት ምክንያት የሚወስዱት ተጨባጭ እርምጃ ይኖራል ብለን አንገምትም። ስለሆነም ሪፓርቱ በኅብረቱና በመንግሥታቱ የኢትዮጵያ ፓሊሲ ላይ ያለንን ቅሬታ የሚለውጥ አይደለም።

የ1997 ምርጫ ታዛቢ ቡድን መሪ ሚስስ አና ጎሜዝ ተመሳሳይ ሪፓርት አቅርበው እንደነበር ይታወሳል። የአውሮፓ ኅብረትና መንግሥታቱ በዚያ ሪፓርት መነሻ ተጨባጭ እርምጃዎችን ወስደው ቢሆን ኖሮ የዘንድሮው አሳዛኝ ድራማ ባልተከሰተም ነበር ብለን እናምናለን።

በጫንቃችን ላይ የተንሰራፋውን ዘረኛና አምባገነን ሥርዓት ማስወገድ የኛ ኃላፊነት ስለመሆኑ የዘነጋንበት ወቅት የለም። ሆኖም ግን የአውሮፓ ኅብረት፣ የአውሮፓ መንግሥታት እና ሌሎችም ዲሞክራሲያዊ አገሮች በሥልጣን ላይ ያለው ሥርዓት ህገ-ወጥ መሆኑን እያወቁ የፋይናንስ፣ የወታደራዊና የመረጃ ድጋፍ እያደረጉለት ትግላችንን አዳክመውብናል። ዲሞክራሲያዊ አገሮች እሴቶቻቸውን በውጭ ጉዳይ ፓሊሲዎቻቸው በተለይም በኢትዮጵያ ፓሊሲዎቻቸው ማየት እንሻለን።

ከዘረኛና አምባገነን ሥርዓት ጋር መወገን የአጭር ጊዜ ጠቀሜታ ያለው ቢመስልም ጉዳቱ እጅግ ከፍተኛ እንደሆነ የአውሮፓ ኅብረትና መንግሥታቱ እንዲያጤኑ አበክረን እናሳስባለን። የአካባቢ ሰላም የሚጠበቀው፤ እውነተኛ የኢኮኖሚ ልማት የሚኖረው፤ ፍትህ የሚሰፍነው የህዝብ ውክልና ያለው መንግሥት ሲኖር መሆኑን ኅብረቱና መንግሥታቱ እንዲያጤኑ እናሳስባለን።

እነሱ በመረጡት መንግሥት መመራት እንደሚሹ ሁሉ የኢትዮጵያ ህዝብም በመረጠው መንግሥት መመራት የሚሻ መሆኑን ልብ እንዲሉ ደግመን ደጋግመን እናሳስባለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## ግንቦት 7 በጥቅምት 98 የወደቁትን ሰማእታት አስመልክቶ መግለጫ አወጣ

ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነት እና የዴሞክራሲ ንቅናቄ በድህረ-ምርጫ 97 በዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ ቀጥተኛ ትእዛዝ የአጋዚ ጦር በንጹሃን ዜጎች ላይ ከፈጸማቸው ጭፍጨፋዎች ውስጥ በጥቅምት 98ቱ የወደቁትን ሰማእታት ለማሰብ መግለጫ አውጥቷል።

ንቅናቄው ባወጣው መግለጫ፥ በጥቅምት 98 የወደቁትን በአስርት የሚቆጠሩ ንጹሃን ዜጎች ስናስብ፤ እነሱ የጀመሩትን ጉዞ ለመጨረስ ቃላችንን ማደስ አለብን ብሏል። ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ የግንቦት 1997ቱን ምርጫ ከሰረቀ በኋላ፤ የህዝብ ድምጽ ይከበር ብለው የተነሱ ንጹሃን ዜጎችን በሰኔ ወር እና በተከታዩ ጥቅምት በጭካኔ ማስጨፍጨፉ ይታወሳል።

ብዙዎቹን የግፍ ግድያዎች የፈጸመው እና በብዛት ከአንድ ብሔር በተውጣጡ ሰዎች የተዋቀረው የአጋዚ ጦር በወቅቱ የተልእኮውን ትእዛዝ ሲቀበል የነበረው ከዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ እንደሆነ ይታወሳል።

መለስ ዜናዊ ከምርጫው በኋላ ባሉት ወራት በንጹሃን ላይ ስለተካሄደው ጭፍጨፋ ሃዘን ይሰማው እንደሆን ተጠይቆ፤ በወቅቱ የተወሰዱት እርምጃዎች በፖለቲካ ስሌት ላይ ተመስርተው እንደሆነና ምንም ቁጭት እንደሌለው መናገሩ ይታወሳል። በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች እና በሶማሊያ ለተፈጸሙ የጅምላ ግድያዎች እጃቸው ያለበት እና ወደፊት አለማቀፍ ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ ምርመራ እየተደረገባቸው ካሉ የወያኔ ባለስልጣናት ውስጥ አንዱ የዘረኛው አገዛዝ ቁንጮ እራሱ መለስ ዜናዊ እንደሆነ ከዚህ ቀደም መዘገባችን ይታወሳል።

ግንቦት 7 ባወጣው መግለጫ፣ የቀድሞ ትውልዶች ለነጻነታቸው ከፍተኛ መስዋእትነት በመክፈል እንዳለፉ አስታውሶ፤ እነሱ የከፈሉት ዋጋ ግን ሁሌም በአዲስ ዋጋ ሊታደስ ይገባዋል ብሏል።

በተያያዘ ዜና፥ ለሰማእታቱ አለማቀፍ መታሰቢያ ዝግጅቶችን እያሰናዳ ያለው ግብረሃይል በለቀቀው መግለጫ፣ ጥቅምት 98ን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከታዩ የጨለማ ወቅቶች አንዱ ብሎታል። ግብረሃይሉ በዋሽንግተን ዲሲ የመታሰቢያ ስብሰባ እንደተዘጋጀም ይፋ አድርጓል።

## በድህረ-ምርጫ 97 የወደቁትን ሰማእታት ለማሰብ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ዘረኛው እና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ ላይ የሚያካሄደውን ዘረፋ የሚጋልጥ መጽሃፍ በቅርቡ ያሳተሙት እና ለረዥም አመታት የአለም ባንክ ሰራተኛ የነበሩት ኢኮኖሚስት ዶ/ር አክሎግ ቢራራ፤ በውጭ አገር ያሉ ኢትዮጵያውያን ቢያንስ የወያኔን አገዛዝ የውጭ ምንዛሬ በመከልከል ትልቅ ስራ ሊሰሩ እንደሚችሉ መክረዋል።

የግንቦት 7 ንቅናቄ እና የጥምረት ለነፃነት፣ ለእኩልነት እና ለፍትህ በኢትዮጵያ ሊቀመንበር የሆኑት ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በበኩላቸው ግድያዎቹ በተካሄዱበት ጊዜ የሆኑ ክስተቶችን፤ በወቅቱ ሰላምን ለማውረድ ከገዢው ቡድን ጋር የተሞከሩ ውጤት አልባ ድርድሮችን አስታውሰው፤ የአገዛዙ ቁንጮዎች “ምርጫቸው ከስልጣን መውረድ እና ኢትዮጵያን ማጥፋት ቢሆን፤ ኢትዮጵያን ከማጥፋት ምንም ወደ ኋላ የምይሉ ናቸው…” ሲሉ መደምደማቸውን ገልጸዋል።

“ጄኖሳይድ ዋች” የተባለው እና በአለማችን ዙሪያ የሚካሄዱ የዘር ማጥፋት ወንጀሎችን የሚከታተለው ድርጅት መሪ የሆኑት ዶ/ር ግሬጎሪ እስታንተን፤ ኢትዮጵያውያን ቢደራጁ የወያኔን አገዛዝ መገልበጥ ከባድ እንዳልሆነ አስረድተዋል። ዶ/ር ግሬጎሪ ጨምረውም፥ በኢትዮጵያ ግፍ የሚፈጽሙት ግለሰቦች አንድ ቀን ወደ ፍርድ መቅረባቸው ስለማይቀር፤ ሁሉም ሰው ስማቸውን በመጻፍ እና መረጃ በማሰባሰብ እንዲሳተፍ ጥሪ አቅርበዋል።

የመታሰቢያ ዝግጅቱ አስተባባሪ ግብረሃይል በበኩሉ በኢትዮጵያ የሚካሄዱ የግፍ ግድያዎችንና ጭፍጨፋዎችን የሚመመዘግብ፣ “www.ethiopianmassacre.com” የተባለ ዌብ ሳይት መከፈቱን አስታውቆ፤ ኢትዮጵያውያን የሚያውቋቸውን መረጃዎች ወደዚህ ማህደር በመላክ እንዲረዱ ጥሪ አድርጓል።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታሳጥን ቁጥር ፡- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

## በአንድ ስፍራ የሚፈጸም ኢ-ፍትሃዊነት፣ በየትኛውም ቦታ ላለ ፍትህ አደጋ ነው

*ከዝግጀት ክፍላችን*

ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ ቡድን፣ "ጅቡ አማራ መጣብህ" እያለ የትግራይን ህዝብ ማስፈራራትን እና ከጉያው ማስገባትን እንደ ፖለቲካ ስልት ሲጠቀም አስርተ አመታት ተቆጥረዋል። ይህ ስሌት አገዛዙ እድሜውን እንዲያራዝም ሲረዳው፤ የትግራይ ህዝብ ወደፊት ሊገጥመው ስለሚችለው አደጋ ያለውን ስጋት ግን እያባባሰው ሄደ እንጂ አልቀነሰውም።

በድህረ-ምርጫ 97፥ የወያኔ አገዛዝ "አማራ ሊያጠፋችሁ ነው" ብሎ ለትግራይ ተወላጆች የሰበከው ስብከት በትግራይ ምሁራን እና ልሂቃን ዘንድ ፈጣን ተቀባይነት ማግኘቱ ብዙዎችን አስደንግጦ ነበር። ምንም እንኳ የትግራይ ክልል እና ተወላጆች በወያኔ አገዛዝ አማካኝነት እንደሚጠቀሙ ብዙ ቢወራም፤ ከአገዛዙ ይልቅ ለትግራይ ህዝብ ጥቅም ይቆም የነበረው የተቀረው ኢትዮጵያዊ ነበር። ለዚህ የሚሆኑ ማስረጃዎችን ጠቅሶ ወደፊት ማስረዳት ይችላል።

ዘረኛው አገዛዝ በአገሪቱ ውስጥ ለሚያካሄደው ግፍ እና አፈና ሆን ብሎ የትግራይ ተወላጆችን መጠቀሙ፤ በተለይ በትምህርት ቤቶች እና በተለያዩ ስፍራዎች የስለላ ስራ የሚሰሩ የትግራይ ተወላጆች ጓደኞቻቸውን አሳልፈው ሲሰጡ እንዲታዩ መደረጋቸው የቂም፣ የቁጣ እና የበቀል ስሜቶችን ስለመፍጠሩ ጥያቄ የለውም። በንግድ እና በፖለቲካ ስልጣን ክፍፍልም ከመንግስት ተቋማት በሚደረግላቸው ልዩ ድጋፍ በብዛት እየተጠቀሙ ያሉት ትግራውያን በመሆናቸው ስር የሰደደ ቅሬታ መብቀል ከጀመረ ቆይቷል።

እነዚህ ስሜቶች ተፈጥሯዊ እና አዎንታዊም ናቸው፤ እየተሰራ ያለው ነገር ትክክል አለመሆኑን እናውቃለን ማለት ነው። በህዝብ ንብረት እና ተቋማት ውስጥ እንዲህ ያለ የአድሎ ስራ ሲሰራ መቆጣትም ተገቢ ነው። ስጋት እየፈጠረ ያለው ግን እነዚህ ስሜቶች ወዴት ሊያመሩ ይችላሉ የሚለው ጥያቄ ነው።

አንዳንዶች፥ ወያኔ የፈለገውን ያህል የመከፋፈል ስራ ቢሰራ በሃገራችን ውስጥ የእርስ በርስ ግጭት አይፈጠርም፤ ህዝባችን ለብዙ ዘመናት ተከባብሮ መኖርን የተለማመደ ነው ይላሉ። ይህ የኛም ተስፋ ነው። ይሁን እንጂ፥ ይህንን ደግሞ የሚቃረን አስተያየት የሚሰጡ እና በአገሪቱ ውስጥ በዘር ወይም በሃይማኖት ላይ የተመሰረተ ግጭት ሊቀሰቀስ እንደሚችል የሚያሳስቡ ድምጾች እየተበራከቱ መጥተዋል። ከዚህ ቀደም፥ በተለያዩ የውጭ አገር ተመራማሪዎች የወጡ ጽሁፎችን ጨምሮ፤ በዛሬ የዜና ዘገባ እንዳሰማናችሁ፥ ጄኖሳይድ ዋች የተባለው የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅት ፕሬዚደንት ዶ/ር ግሬጎሪ እስታንተን በግልጽ ቋንቋ ትግራውያን ለወያኔ ሃጢያት ሊከፍሉ ይችላሉ የሚል ስጋት እንዳለባቸው ተናግረዋል። ይህንን አመለካከት የሚጋሩ ኢትዮጵያውያንም ብዙ ናቸው።

ለምሳሌ ያህል ከጥቂት አመታት በፊት በጅማ አካባቢ የተከሰተውን ሃይማኖታዊ ግጭት እና የተካሄደበትን አሰቃቂ አኳኋን ልብ ላለ፤ የምንኖረው በተለየ ጊዜ እንደሆነ፤ እንዲሁም ከመጋረጃው በስተጀርባ የሚቀሳቀሱ እና ግጭትን በመፍጠር የሚጠቀሙ ሃይሎች እንዳሉ ለመረዳት አያዳግተውም። ከነዚህ ሃይሎች ደግሞ ቀንደኛው የወያኔ አገዛዝ እራሱ ነው። የዛሬው ትኩረታችንም በዚሁ ላይ ነው።

ብዙዎች የወያኔ አገዛዝ ሲገለበጥ በትግራውያን ላይ የሚወሰድ የበቀል እርምጃ ሊኖር እንደሚችል ያሳስባሉ። ያ ስጋት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ እኛ ደግሞ የምንጨምረው አለን። ሊያሰጋን የሚገባው፥ የወያኔ የስልጣን ወንበር ሲነቀነቅ በትግራውያን ላይ ከሌሎች ብሔረሰቦች አባላት ሊደርስባቸው የሚችልን ጥቃት ብቻ ሳይሆን፤ በአገዛዙ ራሱ የሚቀናበርን የጭካኔ እርምጃ ነው።

መለስ ዜናዊ እና ጓደኞቹ፥ እስካሁን ከኢትዮጵያ ህዝብ የበዘበዙትን ሃብት ማስቀመጫ እና ልጆቻቸውን ማንገሻ መንበረ ስልጣን ይፈልጋሉ። የኢትዮጵያ ህዝብ "በቃ!" ብሎ በመነሳት ከስልጣን ያባረራቸው ለታም፤ ትግራይን ገንጥሎ አዲስ አገር በመፍጠር ለራሳቸው እና ለእኩይ ህልማቸው መሸሸጊያ ምሽግ ለመፍጠር እንደሚሞክሩ የብዙዎች ግምት ነው። ይህን ህልማቸውን እውን ለማድረግ ደግሞ የትግራይን ህዝብ ድጋፍ ማግኘት የግድ ነውና፤ ትግራውያንን ከተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር በማያዳግም ሁኔታ ሊያጣሉ የሚችሉበት አንድ መንገድ ቢኖር ከፍተኛ ፍጅት ማቀናበርን ነው። እንዲህ አይነቱ እልቂት እና ተከትሎት የሚመጣው ቅራኔ ደግሞ ህዝቡ ከሌላው ኢትዮጵያዊ የተለየ ማንነት እንዲሰማው የሚያደርገው ሲሆን፤ ይህ ለወያኔ ቁንጮዎች ታላቅ ድል ነው። በመለስ ዜናዊ የሚመራው ገዢ ቡድን፣ ይጠቅመኛል ብሎ ካመነ እንዲህ ያለን ጭካኔ ከመፈጸም ወደ ኋላ የሚል እንዳልሆነ ደግሞ ያለፈ ታሪኩ ያመለክታል።

ስለዚህም፥ የትግራይ ህዝብ እና ልሂቃኑ፥ "በአንድ ስፍራ የሚፈጸም ኢ-ፍትሃዊነት፣ በየትኛውም ቦታ ላለ ፍትህ አደጋ ነው" የሚለውን አባባል አንግበው፤ ቀኑ ሳይመሽ እና ምንም መስራት የማይቻልበት ደረጃ ላይ ሳይደረስ በፊት በአገራችን ፍትህን ለማስፈን የሚደረገውን ትግል ሊቀላቀሉ ይገባል።

ያም ሆነ ይህ ግን፥ ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነጻነት እና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ በማንኛውም ጊዜ ቢሆን ለሁሉም የኢትዮጵያ ህዝቦች ደህንነት፣ ፍትህ እና መብት የሚቆም፣ የሚሟገት፣ የሚታገል እና የሚከላከል መሆኑን ደግሞ እና ደጋግሞ ሊያስረግጥ ይወዳል።

## የወያኔ አገዛዝ የአዲስ አበባን ህዝብ ለመበዝበዝ የሚያደርገው ስንድት ምሬት ቀሰቀሰ

የአዲስ አበባ መስተዳደር፥ የመጪው አምስት አመታት እቅዱን በገንዘብ በመደገፍ ስም ነዋሪው ስድስት መቶ ሚሊዮን ብር እንዲያዋጣለት እቅድ አውጥቶ እየተንቀሳቀሰ መሆኑ ተዘግቧል።

የግንቦት 7 ድምጽ ሪፖርተር ከአዲስ አበባ በላከው ተከታይ ዘገባ፥ አንዳንድ ነዋሪዎች፣ "ልጆቻችንን የምናበላው አጥተን ባለንበት ዘመን ከየት አምጥተን እንድንሰጣቸው ፈለጉ?" ሲሉ ተደምጠዋል። በከተማይቱ ውስጥ ሰባት መቶ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ማእከላት መመስረታቸውን የገለጸው ዘጋቢ፤ ነዋሪዎች ስብሰባ ቢጠሩም ከካድሬዎች በስተቀር አብዛኛው ህዝብ እንዳልተገኘ አመልክቷል።

የአዲስ አበባ የገቢ ቢሮ፥ ህዝቡ ገንዘቡ ምን አይነት ጥቅም ላይ እንደሚውል እና በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉን እንዲረዳ የከተማይቱን በጀት በዝርዝር ለህዝብ ማሳወቁን ተናግሯል። ይሁን እንጂ፥ ይህንን በሚመለከት ዘጋቢያችን ያናገራቸው ዜጎች፣ ይህ አገዛዙ ተጠያቂነት እንዳለ በማስመሰል ህዝቡን ለመዝረፍ ያዘጋጀው ማታለያ ነው ብለዋል።

የሚሰጡት ገንዘብ እንደሌላቸው የሚናገሩት ነዋሪዎች፤ ኖሯቸው ቢሰጡ እንኳ የት እንደሚሄድ እንደሚያውቁ እና ያም ወደካድሬዎቹ ኪስ ነው ሲሉ ገልጸዋል። ከዚህ የሚጠቀሙት የወያኔ ካድሬዎች ራሳቸው ስለሆኑና፣ የህዝብን ሃብት በመበዝበዝ የከበሩትም እነሱው በመሆናቸው፤ አስተዳደሩ እነሱኑ ቢጠይቅ ይሻለዋል ሲሉም አስተያየት ሰንዝረዋል።

## በኖርዎይ ኦስሎ ሂዩማን ራይትስ ዋች . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ሌፍኮ ከኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዲስ አበባ ጀምሮ እስከ ዝቅተኛ የወረዳ ገጠር ቀበሌዎች መዘዋወራቸውን ጠቅሰው የራሳቸውን ተሞክሮና መረጃ በመመርኮዝ ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያዊያን ላይ እያደረሰ ያለውን በደል በዝርዝር አስረድተዋል። በማብራሪያቸው መጨረሻም ምእራባዊያን ለጋሽ ሃገራት ለአገዛዙ የሚለግሱት ገንዘብ ለፖለቲካ ፍጆታ መዋሉንና በኢትዮጵያ የሰባዊ መብቶች ጥሰት እጅግ በሚገርም ሁኔታ እየተባባሰ መሄዱ እየታወቀ በተቃራኒው የለጋሽ ሃገራት ርዳታ ደግሞ በእጥፍ መጨመሩን አስረድተዋል። ሌፍኮ ይህ ምን አንድምታ እንዳለውና ምንስ መልእክት እያስተላለፉ እንደሆነ ጥያቄውን መመለስ ያለባቸው ራሳቸው ለጋሽ ሃገራቱ ናቸው በማለት አጠቃለዋል።

በቀረበው ሪፖርት ላይ ሰፊ ውይይት፣ ክርክርና በተለይም በእለቱ ስብሰባው ላይ ከተሳተፉ  ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን እልህና ቁጭት በተሞላበት መልኩ በኢትዮጵያ እየታየ ስላለው አስከፊና አሳዛኝ ሁኔታ ተጨማሪና ማጠናከሪያ መረጃዎች ተሰጥተዋል። ኢትዮጵያዊያኑ ኖርዎይን ጨምሮ ምእራባዊያን ሃገራት የልማት ርዳታ እያሉ የሚልኩትን ገንዘብ የወያኔው አገዛዝ የጥይት መግዣና ወገኖቻችንን ማስጨረሻ እያደረገው እንደሆነ ሊያውቁና አስቸኩአይ የሆነ ርምጃም ይወስዱ ዘንድ ጠይቀዋል።

## የኦጋዴን ብሔራዊ ነጻነት ግንባር 267 የወያኔ ወታደሮችን ገድያለሁ ማለቱ ተዘገበ

ለረዥም አመታት የወያኔን አገዛዝ ሲዋጋ የቆየው የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር (ኦብነግ) ባለፉት በርካታ ሳምንታት በአገዛዝ ጦር ላይ በከፈተው ጥቃት 267 ወታደሮችን መግደሉን እና 157 ማቁሰሉን እንደገለጸ ሬውተርስ የዜና አገልግሎት ድርጅት ዘግቧል።

የአገዛዙ ቃል አቀባይ ሽመልስ ከማል ጥቃቱ መፈጸሙን እንደ ወትሮው ክዷል።

ኦብነግ ሶማሊ ክልል ውስጥ ተደጋጋሚ ጥቃቶችን የሚፈጽም ሲሆን፤ ቡድኑን ማጥፋት ያቃተው የወያኔ አገዛዝ ጋዜጠኞች ወደ አካባቢው ተጉዘው የሚደርስበትን ጥቃት እንዳይመዘግቡ ከከለከለ አመታት ማስቆጠሩ ይታወቃል።

በአካባቢው የነዳጅ ዘይት እና ጋዝ ፍለጋ ሲንቀሳቀስ የነበረው የማሌዥያ ኩባንያ ፔትሮናስ ይዞታውን ለሌላ ኩባንያ ሸጦ መውጣቱ ይታወቃል። በአሁኑ ሰዓት አገዛዙ በሽያጩ እንዲስማማለት እየጠበቀ ነው ሲል ሬውተርስ በዘገባው አመልክቷል። ፔትሮናስ የማእድን ፍለጋ ፕሮጀችቱን ትቶ ለመውጣት የተገደደው ወያኔ በአካባቢው ጸጥታን ማስፈን ስለተሳነው ነው ሲሉ አስተያየት ሰጪዎች ይናገራሉ። ኦብነግ ከዚህ ቀደም ባወጣው መግለጫ፤ የፔትሮናስን ይዞታ የገዛው ኩባንያ ከአገዛዙ ጋር ግንኙነት አለው ማለቱ ይታወሳል።

## ወያኔ ሰሞኑን በቢቢሲ ላይ የከፈተው የቃላት ጥቃት፥ የአገዛዙን የውሸት ባህል ለአለማቀፉ ማህበረሰብ አጋልጧል ተባለ

ታዋቂው የብሪታንያ የመረጃ አውታር ቢቢሲ ከበርካታ ወራት በፊት ዘረኛው የወያኔ ቡድን ጫካ በነበረበት ወቅት በርሃብ ይጠቃ በነበረው የትግራይ ህዝብ ስም የሰበሰበውን እርዳታ ለጦር መሳሪያ ግዢ አውሏል ብሎ መዘገቡ ይታወሳል።

የወቅቱ የቢቢሲ ዘገባ ስኮትላንዳዊው ቦብ ጌልዶፍ በ1977 የኢትዮጵያን ረሃብተኞች ለመርዳት ያደረገውን የገንዘብ ማሰባሰብ በዘገባዎቹ እንደ ማስረጃ በመጠቀሙ፤ ታዋቂው አቀንቃኝ ቢቢሲን ለሚያስተዳድረው ቦርድ ስሞታ አሰምቷል። ያንን ተከትሎ ከተደረገው የማጣራት ስራ በኋላ፤ ቢቢሲ የቦብ ጌልዶፍ ድርጅት ላይ ያነጣጠረ ዘገባ ማቅረቤ ትክክል አይደለም ብሎ ይቅርታ የጠየቀ ሲሆን፤ ወያኔ ከእርዳታ ድርጅቶች የሰበሰበውን ገንዘብ ለጦር መሳሪያ መግዣ አውሏል በሚለው አቋሙ ግን እንደጸና መሆኑን ገልጿል።

ይሁን እንጂ ይህንን ዜና ተከትሎ በወያኔ አገዛዝ ቁጥጥር ስር ያሉ የዜና አውታሮች እና የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ሆን ብለው የተዛባ መረጃ ለህዝብ እያቀረቡ ነው። የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድርጅት፥ ቢቢሲ ለእርዳታ የተሰበሰበ ገንዘብ ለጦር መሳሪያ ግዢ ውሏል ብሎ በመዘገቡ ይቅርታ ጠይቋል ብሎ እየዋሸ ሲሆን፤ የበረከት ስምኦን ቢሮ ደግሞ የዜና ተቋሙ ሚስተር ጌልዶፍን ይቅርታ እንደጠየቀ የኢትዮጵያንም መንግስት ይቅርታ ሊጠይቅ ይገባዋል ብሎ መግለጫ አውጥቷል።

የወያኔ ባለስልጣናት በማናለብኝነት የሚገዙ ስለሆኑ የአገርን ጉዳይ የሚያዩት እንደ ልጅ ጫወታ ነው ያሉን አንድ የፖለቲካ ተንታኝ፤ "አገር ቤት ያለው ህዝብስ መረጃ አያገኝም በሚል አስተሳሰብ ቢዋሹት አንድ ነገር ነው፤ ለአለማቀፉ ማህበረሰብ ፍጆታ ይውል ዘንድ በጉዳዩ ላይ በእንግሊዝኛ መግለጫ ማውጣታቸው የራሳቸውን የውሸት ባህል የሚያጋልጥ ነው" ብለዋል። ጨምረውም፥ "የአለማቀፉ ማህበረሰብ ቢቢሲን እንጂ እነሱን እንደማያምን እየታወቀ የኢትዮጵያን ህዝብ እንደሚያደርጉት ለማታለል መሞከራቸው አስቂኝ ነው" ሲሉ አስረድተዋል።

## የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢዎች ቡድን . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የቆጠራ ሂደቱም ግልጽነት የጎደለው እንደነበር አስረድቷል። የታዛቢዎቹ ቡድን ሪፖርቱን ይፋ ማድረጉን ተከትሎ ጋዜጣዊ መግለጫ ያወጣው አለማቀፍ የሰብአዊ መብቶች ተሟጋች "ሂውማን ራይትስ ዋች"፤ "እውነታዎቹ ለራሳቸው ይመሰክራሉ፦ አገዛዙ በግንቦት ወር 99.6 በመቶ የሚሆነውን መቀመጫ አሸንፌያለሁ ማለቱና፤ ሌላው ቀርቶ የታዛቢ ቡድኑ ሪፖርቱን አዲስ አበባ እንዲያቀርብ መፍቀድ አለመፈለጉ፥ ስር የሰደደውን ተቃውሞ እና ሂስ ያለመቀበል ባህሪውን ያጋልጣል" ብሏል።

"ሂውማን ራይትስ ዋች" ጨምሮም፥ ምርጫው ሊካሄድ ጥቂት ሳምንታት ሲቀሩት፥ የአገዛዙ ካድሬዎች እና ሚሊሻዎች ከቤት ቤት እየተዘዋወሩ ህዝቡ ገዢውን ቡድን እንዲመርጥ፤ ካልመረጠም እንደሚቀጣ እና፤ ይህም ቅጣት መኖሪያን ወይም ስራን መነጠቅን እንደሚያካትት እንደተነገረው ገልጿል።

## የየረር ዋሻ ገዳም እስካሁን በወያኔ ፌዴራል ፖሊስ ተከቦ እንደሚገኝ ታወቀ

በሶስት አመት ውስጥ የወያኔን አገዛዝ የሚተካ መሪ ይነሳል ብለው አንድ ባህታዊ በመተንበያቸው በዘረኛው አገዛዝ ወታደሮች የተወረረው ገዳም በወያኔ ፌዴራል ፖሊስ አባላት እየተጠበቀ ነው ሲል የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን - ኢሳት - ዘግቧል።

የትንቢቱን መነገር ሲሰማ ገዳሙን ያስወረረው ዘረኛ አገዛዝ ባህታዊያንን ማስደብደቡን እና በድብደባውም የሞቱ እንዳሉ ይሸሽጉ የዜና አውታር ጠቅሰን መዘገባችን ይታወሳል። ወደ ስፍራው ተጉዞ የማጣራት ስራ የሰራው የኢሳት ዘጋቢ በደም የተጨማለቀ የአንድ ባህታዊ ልብስ ማየቱን ገልጿል።

በደብረ ዘይት አድርገው ወደ የረር ባታ ማሪያም ገዳም የሚሄዱ ምእመናን በፌዴራል ፖሊስ አባላት ፍተሻ እና ክትትል እየተደረገባቸው እንዳለ የጠቀሰው ዘገባ፤ ረዳት ያጡት ሰላማዊ ባህታውያን በፍርሃት ውስጥ እንዳሉና የሚደርስባቸው እንግልትና ወከባ እንዳላቆመ አትቷል።

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ወደ ቤተእምነት ዘልቆ ገብቶ በምእመናን ላይ እንዲህ ያለ ጥቃት የሚፈጽም አገዛዝ ታይቶ አይታወቅም ያሉን አስተያየት ሰጪ፤ እንዲህ ያለው ተግባር የሚፈጸመው በወራሪ ሃይሎች ብቻ ነው ብለዋል። አሁን ስልጣን ላይ ያለው ቡድን አባላት ጫካ በገቡባቸው የመጀመሪያ አመታት በትግራይ ቤተክርስቲያናት ውስጥ ከነጫማቸው እየገቡ ይጨፍሩና ሆን ብለው ያረክሱ እንደነበር ያስታወሱት ግለሰብ፤ የገዢውን ቡድን ማንነት ለሚያውቅ ግን የሚሰሩት ስራ አያስገርምም ብለዋል። ኢትዮጵያውያን ለባህታውያኑ ከመጸለይ አንስተው በተቻላቸው መጠን እየተፈጸመባቸው ካለው ጥቃት በመከላከል እንዲረዷቸውም ጥሪ አቅርበዋል።

## በርካታ የፌደራል ፖሊስ አባላት በዘረኛነት ምክንያት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ፖሊሶች፣ ማንበብና መጻፍ በቅጡ የማይችሉ የአንድ ብሄር አባላት ዲፕሎማና ዲግሪ ያላቸውን የሌላ ብሔር አባል ፖሊሶች እንደሚያዙ ተናግረዋል።

እድገት ለማግኘት የተወሰኑ ብሄር ተወላጆችን ታማኝነት ማግኘት ይጠይቃል የሚሉት ፖሊሶች፣ ሁኔታው ለመቋቋም ከሚችሉት በላይ ሲሆንባቸው እንደሚለቁ ኢሳት ዘጋቢውን ጠቅሶ ዘግቧል። በጉዳዩ ዙሪያ የፌደራል ፖሊስ ባለስልጣናትን ለማግኘት ያደረገው ጥረት እንዳልተሳካለትም የዜና አውታሩ ገልጿል።

ኢትዮጵያ ውስጥ፥ የመንግስትን ስልጣን በዋነኛነት የሚቆጣጠሩት እና በተለይ በመከላከያ እና የህግ አስከባሪ ተቋማት ውስጥ ቁልፍ ቦታዎችን የያዙት ጥቂት የትግራይ ተወላጆች እንደሆኑ ይታወቃል። የግንቦት 7 ድምጽ ከዚህ ቀደም ባወጣው ሰፊ ሪፖርት ከ60 የመከላከያ ቁልፍ መቀመጫዎች ውስጥ 57ቱ በትግራይ ተወላጆች መያዛቸውን ማጋለጡ ይታወሳል። በጦሩ ውስጥ፥ በውትድርና አሰራር ተቀባይነት በሌለው መልኩ፤ ዝቅተኛ የስልጣን ደረጃ ያላቸው ትግሬውያን የበላያቸው የሆኑ የሌላ ብሔር ተወላጆችን እንደሚያዙ፣ እንደሚሰድቡ እና በግልጽ እንደሚያዋርዱ ተደጋጋሚ ስሞታዎች ይሰማሉ።


## የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት እስከ 3:30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2:30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቂያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org